# ምላሽ ለአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ (ሃማ ቱም)

በተከታታይ የነበርነው እንጻፍና፣ ከጠላፊው ለጠላፊው እንዲሁም ሳያጣሩ ወሬ.. ዋለልኝና ያን ትውልድ ለቀቅ በተሰኙት እርእስት ያቀረብከውን መጣጥፍ በጥንቃቄ ተመልክተን ይህን ምላሽ ለመጻፍ ተገደናል።

የኢሕአፓ መሥራችና የሞት ትራፊ ሆነህ ሳለ ዛሬም እንኳን እንበለ ጸጸትና ግንዛቤ ቡራ ከረዩ ስትልና ትርኪ ምርኪ መዘላበድህን ስንሰማ እጅግ በጣም ያሳፍራል። ለነገሩማ ስደት ለወሬ ይመቻል እንዲሉ በውጭ መኖር መልካም አጋጣሚ ከሞት የተረፍክ ቢሆንም እንኳ ዛሬም ዓይንህን በጨው አጥበህ ስትቀላምድ ማየትና መስማት በጣም ያስተዛዝባል። ስለምን ቢባል እኛም በአገር ቤት በዚያን ጊዜ በወጣትነት እድሜያችን ከሁለተኛ ደረጃ እስከ የቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በነበርንበት ከየካቲቱ 1966 ዓ.ም አብዮት በፊትም ሆነ በኋላ በእድገት በሕብረት ዘመቻ ሁሉ ከሌሎቹ ጓደኞቻችን ለምሳሌ ከግርማቸው ለማ ኪዳኔ ቡድን ጋራ በመሆን የከፈልነውን መስዋእትነት ስናስበው ዛሬ የሚሰማኝ ጥልቅ ሃዘንና ጸጸት ወሰን የለውም። ታዲያ! አንተና ብጤዎችህ እንደ ተልባ በመንጣጣት የተጀመረውን የጥፋት ሂደት ተዋናያን ማንነት የደረሰውን ከፍተኛ ሕብረተሰባዊ ቀውስ በሚተቹት ወገኖች ላይ ለምን ሐቁ ይወጣል ሥጋትና ፍርሃት እንበለ እፍረትና ሕሊናቢስነት አፍ ለማዘጋት፣ ታስቦ የሚደረገው ከንቱ መንበላጠጥ ከቶ ምን ይባላል!

በአለፈው ዓመት አቶ አስፋ ጫቦ በኢሳት መገናኛ ቀርቦ የሰጠውን ቃለ መጠይቅ አስመልክቶ እጅግ በጣም አሳፋሪው ትረካህ ላይ፣

"የበቃለት ሬሳን ሁሉ ቀስቅሶ ቃልና መድረክ መስጠት የለመደበት አንድ የራዲዎና ቴሌቪዥን ጣቢያ ሞት ራሱ ሊወስድ የተጠየፈውን ወንጀለኛ አዛውንት ለመድረክ አቅርቦ በሐቅና በኢሕአፓ ላይ ......"

እያልክ አቅርበኋል። አንተ በውጭ በሽሽት ተሰደህ ስለምትኖር ከሞት አምልጠህ ዘላለም የምትኖር መሰለህ? ያንተንስ ወንጀለኛነት የተረሳ ይመሰልሃል?

ሰሞኑን ደግሞ ሐቀኛው ኢትዮጵያዊ አርበኛ ጌታቸው ረዳ ስለ ጸረ ዐማርዎች ማንነት ያቀረበውን ጥናታዊ ጽሑፍ አስመልክቶ ዋለልኝ መኮንን አትንኩብኝ ብለህ በግጥም ተብዬ ቅላጼ የተሸፋፈነውን ግን በጣም ያረጀ ያፈጀ የጎሣ ፖለቲካ አቀንቃኝነትህን በሚመሰክረው ጽሑፍ ላይ <<..**የትምክህት አባወራ ሆነው፣ የሞረሽ አዘጋጅ ሆነው በጭቁን ሕዝብ ላይ የሚጨፍሩ የነበሩት፣ ዛሬም ኦሮሞን ሕዝቡ በሚፈልገው ስም መጥራት የሚያማቸው...**>> በማለት ያሰፈርከው ምን ያህል የጥላቻ ፖለቲካ በደም ሥርህና ጅማትህ ጠልቆ እንደገባና የሕሊና መቃወስ ከእርጅና ጋራ ያደረብህ ስለሆነ ፍጹም አረመኔያዊና ኢሰባዊ አውሬ ባሕርይ የሚያናውዝህ ግለሰብ መሆንክን ፍንትው አድርጎ ያስረዳል። ቀኑ ሳይመሽብህ በጣም በአስቸኳይ ሐኪማዊ ርዳታና እንክብካቤ እንደሚያስፈልግህ በአጽንኦት ማሳሰብ ግድ ብሏል።

# ስለ አውሮፕለን ጠለፊው

በመጀመሪያ ስለ አውሮፕላን ጠለፋው ሌሎች የጻፉትን ቀጥለን እንመልከተው።

፩ኛ ብርሃነ መስቀል ረዳ ለደርግ መርማሪ በሰጠው ቃል በ1961 ዓ.ም ነሐሴ 5 ቀን ባሕርዳር ከሚገኘው አየር ማረፊያ ከስድስት ባልደረቦቹ ማለትም 1ኛ ኃይለ የሱስ ወልደ ሰንበት 2ኛ ዓማኑኤል ገብረ የሱስ 3ኛ ብንያም አዳነ 4ኛ አብዲሳ አያና 5ኛ ኢያሱ ዓለማየሁ 6ኛ ገዛኸኝ እንዳለ ጋራ በመሆን ዲሲ 3 አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን ካርቱም መግባታቸውን አስረድቷል።

በመቀጠልም በሱዳን አገር ከነሐሴ 1961 ዓ.ም እስከ የካቲት 1962 ዓ.ም በካርቱም ፖሊስ አካዳሚ በጥበቃ ሥር መቆየታቸውንና የአልጀሪያ መንግሥት የፖለቲካ ጥገኝነት ስለሰጣቸው ወደዚያ መሄዳቸው፤ በቀይ መስቀል ርዳታ ተደርጎላቸው ትምህርት ቤት እንደገቡና ከአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪ እነ ዶክተር ኃይሌ ፊዳ ጋር ግንኙነት መፈጠሩን ተዘግቧል። ከዚያም በኋላ ልዩ ልዩ ቡድኖችን በማስተባበር ኢሕአድ የተሰኘውን ኮምኒስት ፓርቲ በምዕራብ ጀርመን በርሊን ከተማ መመሥረታቸው ታወቋል።

እዚህ ላይ አንድ የተሸፈጠ ዐቢይ ነገር አለ። ኢያሱ ዓለማየሁ ከመሞትህ በፊት ሐቁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ መናገር ይኖርብሃል።

ይኸውም አውሮፕላኑን ጠላፊችሁ ካርቱም ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥታችኋል። በጋዜጣዊ መግለጫ የኤርትራን ተገንጣይ ቡድን ጀብሃን ማለትም የኤርትራ አርነት ግንባር (ELF) ዓላማና ግብ ደጋፊ መሆናችሁን አሳውቃችሁ ነበር። ለዚህም ማስረጃውም ይኸው።

" As for the university students who hijacked the Bahir Dar- Addis Ababa flight and then declared their support of the goals of the **Eritrean separatists**...."

(Robert L. Hess: Ethiopia the rnodernization of Authocracy, Cornell University Press, 1970, P.190)

ኢያሱ በርግጥም ያልዋሻከተው ቢኖር በሱዳን ካርቱም የተቀበላቸው ኪዳኔ የተባለ የጀበሃ ተወካይ መሆኑን ነው። በአልጀሪያ እያሉም ከጠላፊዎቹ አንዱ ኤርትራዊው ዓማኑኤል ገብረየሱስ የኤርትራን አርነት ግንባርን ሁሉም እንዲቀላቀሉ ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ሳይሳካለት ሲቀር እርሱ ራሱ ብቻውን ወደ መጣበት ከኤርትራ ግንባር መቀላቀሉን ክፍሉ ታደሰ አረጋግጧል።

# <u>ጀበሃ ማን ነው?</u>

ጀበሃ ማለትም የኤርትራ አርነት ግንባር በግብፅ ወታደራዊ መንግሥት መሪ ጀማል አብድል ናስር እና የመላው አረብ ብሔረተኛነት አቀንቃኞች ርዳታ ካይሮ ላይ የተመሠረተው ፌድድረሽኑ ከመሰረዙ አስቀድሞ እንደነበር የተረጋገጠ ነው። መጠነ ሰፊ ርዳታና ዕውቅናን የሚያገኘውም ከአካባቢው የአረብ አገሮች እንደ ሳውድ አረቢያ፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ ሊባኖን፣ አልጀሪያ፤ ሱዳን፣ የመን እንዲሁም ከፓኪስታን በአረብነትና የእስልምና ሃይማኖት ሽፋን ፀረ ኢትዮጵያዊነት አራማጅ ቅጥረኛ ድርጅት ነበር ።

ጀብሃ በኤርትራ ምድር ከፍተኛ ወታደራዊ ሽንፈት ሲደርስበት በውጭ አገርና በኢትዮጵያ ውስጥ ሽብር መፍጠር ጀመረ።

ስለዚህም ጉዳይ ተገቢውን ማስረጃ እንጠቅሳለን፤

"In June 1965, Ethiopian government newspapers condemned Syria for shiping arms to dissident Eritreans. The Eritrean Liberation Front claimed the death of hundreds of Ethiopian troops, while the Ethiopian government claimed the capture of thousands of ifles of Russian, Czech, Britsh, and even Spanish origin. In December, 1965 Osman Saleh Sabbe, called upon Arab and Muslim states to help Eritrea in its fight for freedom (African Report, February 1966, P .28)

On March 11th 1969, ELF bombed and heavily damaged an Ethiopian Air Linrs jet plane at Frankfurt Air port in West Germany. Encouraged by its sucess at hitting vulnearble Ethiopian targetes abroad, ELF attacked and badly damaged a second Ethiopian jet airliner at **Karachi** Airport two months latter, while other Front agents in the French Teritory ofAfar and Issa atacked the Etiopian Embassay in Djibiti, blew up a section of the Addis Ababa-Djibuti railway and destroyed several locomotives.

In August the guerrillas staged their first hijacing and forced a DC-3 Bahr Dar-Addis domestic flight to detour to Kharthum; the following month they hijacked a Djibuti-bound DC-6 shortly after taking off from Addis and orderd the captain to take them to Aden. Other Front activities in Eritrea itself included disruption of Asmera water supply, raids on police outsposts and destruction of petrolium tank -trucks. " (Ibd , pp 178- 196)

ያውሮፕላን ጠለፋው ለጅብሃ በተከታታይ ሲሳካለት ቆይቶ በ3ኛው ሙክራ ግን ከሽፈበታል።

በታህሣስ ወር 1964 ዓ.ም ዋለልኝ መኮንን ከነ ግብረ አበሮቹ ማለትም ማርታ መብራቱን፣ ጌታቸው ሃብቴን፣ ተስፋዬ ቢራጋን፤ ዮሐንስ በፈቃዱ፣ ዓማኑኤል የሐንስ የተባለው የኤርትራ አርነት አባል በላይ ታደሰ ቢሚል መታወቂያ አዲስ አበባ ገብቶ የነበረው ሲደመሰሱ ታደለች የተባለችው ብቻ ቆስላ ተርፋለች። ይገባቸዋል።

ዋለልኝ መኮንን የተባለው ወሎዬ ግልገል ባንዳ ፀረ ኢትዮጵያ በሆኑት የቀኃሥ ዩኒቨርስቲ አስተማሪ ተብዬ ሰላይዎች እነ ግሪን ፊልድ፣ ጆን ማርካኪስ የተመለመለው ኩታራ በቀቀን ልክ የኦስትራያ ወይም ነምሳ ናዚ ፀረ ጥቁር ፍራየ ኽር ፕሮቻዝካ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዋዜማ ወቅት <u>አበሻ ጥቁር አደጋ</u> በተሰኛ ርዕስ የነዛውን ፕሮፓጋንዳ ናሙናው በማድረግ ዐማራውን ሕዝብ ለይቶ <<ጨቋኝ ብሔር፣ አነስተኛ ሕዝብና ብቸኛው የገዥ መደብ፣ **ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛነት ውሸት ነው፣** ኢትዮጵያዊ የጋራ ባሕል፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ አገር ወዘተረፈ የለም >> እያለ በሶሻሊዝም ካባ ሲያውናብድና ማንኛውም ተገንጣይ ድርጅት የኢትዮጵያን አጤ መንግሥት ለመጣል እስከተጋለ ድረስ መደገፍ አለበት እያለ በቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ሲቀባጥር የነበረ ግልገል ባንዳ ነው። ኢትዮጵያዊ ብሕረተኝነት ውሸት ነው ከተባለ የአድዋው ድልም ውሸት ነዋ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ ፋሽስትና ጸር ቅኝግዛት የአምስት ዓመታት ተጋድሎ ውሸት ነው?

ኢትዮጵያ የጎሣዎች እስር ቤት ናት በማለት እነ ዋለልኝና ብጤዎቹ እነ ብርሃነ መስቀል ረዳ እንደ በቀቀን ሰምተው ሲያስተጋቡት የነበረው የተውሶ ኮምኒስታዊ ተብዬ ርዕዩት በሲዊዘርላንድ ስድተኛ ሆኖ የቆየውና የጀርመን መንግሥት ሰላይ ቅጥረኛ በመሆን የሩሲያን ዛር ግዛትና መንግሥት ያመሰቃቀለውና ያወደመው ፈላጭ ቆራጩ፣ የቀይ ሽብር ፈጣሪ ሌኒና ተከተዩም ጆሴፍ እስታሊን የፈጠሩትን አንብበው ይከተሉት የነበረው ፍጹም አረመኔያዊ የጭፍጨፋና የሽብር ስርዓት ነው በኢትዮጵያ የዘሩት።

የተማሪ እንቅስቃሴ በተለይም በአልጀሪያ ከአውሮፕላን ጠለፋው መልስ የመሸገውና በብርሃነ መሰቀል ረዳ የሚመራው ፈጽሞ በማይገባቸውና በማያውቁት ጥራዝ ነጠቅ ድግምትና ማነብነብ የብሔር

ጥያቄና ቅራኔ በኢትዩጵያ በሚል ርእስ ጥላሁን ታከለ በተሰኘ የብእር ስም ብርሃነ መስቀል ረዳ ከጀበሃው ምልምል ቅጠረኛ ዋለልኝ መኮንን ቀደም ብሎ በቀ ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀውን ፀረ አማራ፣ ፀረ ኢትዩጵያ የፋሽስት ጣሊያን ፕሮፓጋንድን በመቀጠል ኢትዩጵያ የብሔሮች እስር ቤት ናት ብለው የብሔሮች የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል መብት እናስከብራለን እያሉ ለኤርትራ የመገንጠል እውቅና ሲለፍፉ ነበር።

ብርሃነ መስቀል ረዳ የኢትዩጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት (ኢሕአድ) በሚያዚያ ወር 1964 ዓ.ም በምዕራብ ጀርመን በርሊን ከተማ አራት ቡድኖችን አስተባብሮ ከሁለት ዓመታት መደራደር ከተመሠረተ አራት ወራት በኋላ በኤርትራ ተማሪዎች አጠቃላይ ማኅበር 2ኛ ጉባዔ በሶሪያ ደማስቆ ተደርጎ በነበረው ስብሰባ ላይ ራሱ አርቅቆ ለውሳኔ አቅርቦ የጸደቀው በ18 ድጋፍና በ3 የተቃውሞ ድምች በ5ኛው ተራ ቁጥር "የኢትዩጵያ ተማሪዎችና አብዩታው ምሁራን የኤርትራ ሕዝብን ትግልና የነፃ መንግሥት የመምሥረት መብት ሙሉ በሙሉ የሚደግፉ መሆናቸውን እናረጋግጣለን" ይላል።

በብሔር ጥያቄ የኤርትራ ተገንጣይ ተዋጊ ኃይሎችን ዓላማ ደግፏል። የኡጋዴን ሱማሌዎችን የመገንጠልና ከሱማሌ ጋራ የመዋሃድ ጥያቄ ሕዝቡ ቢሻው ከሱማሌ ጋራ መደባለቅ አለበለዚያም የራሱን መንግሥት የመመሥረት መብት እንዳለው ኢሕአድ ያምናል እያለ ሲለፍፍ አልነበረም?

ታዲያ! ኢያሱና ብጤዎቹ ራሳቸውን ኢሕአፓ ባይ ሁሉ ስለምን ይዋሻሉ? መቼ ነው ኢሕአፓ ለአንድነትና ለኢትዩጵያዊነት መቆም የጀመረው? በመጀመሪያ ከጅበሀ ቀጥሎም ከሻዕቢያ ጋራ ወግኖ ሲርመጠመጥ እንድነበር ግን የተረጋገጠ ነው።

በ1964 ዓ.ም ብርሃን መስቀል ረዳና ክፍሉ ታደስ ከጀብሀ ጋራ ግንኙነት ለመመሥረት ኢራቅ ሄደዋል። በዚያም ኢሕአድን ከኢራቅ መንግሥት ጋራ አስተዋውቀዋል። በዚሁ ዓመት የኢሕአድ መልክተኛ ቤይሩት ሊባኖን በመሄድ ከሳላህ ሳቤ ቡድን ጋራ ግንኙነት መሥርቷል።

ሳላህ ሳቤ ለኢሕአድ የገንዘብ ርዳታም ብቻ ሳይሆን ከሌሎች መንግሥታት ጋራ በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ትብብር አበርክቷል። በተለይም ከፍልስጥኤም ግንባር፣ ከሱማሊያ መንግሥት ጋራ ግንኙነት እንዲፈጥረና ለኢሕአድ አባላት የፓስፖርት በማፈላለግ ያበረከተው ትብብር ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ ሳለ ስለምን አቶ ኢያሱ ዐይኑን በጨው አጥቦ ከጀበሀ ጋራ የነበራቸው ግንኙነት ኢምንት ነበር እያለ ይወሻል?

አገራችን መቀመቅ የገባችው መቼ በወታደራዊ ደርግ ጥርቃሞ ብቻም ሳይሆን ከኢትዩጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መከፋፈል የተፈጠሩት ሁለቱ ቡድኖች ራሳቸውን መኢሶንና ኢሕአድ /ኢሕአፓ/ ብለው በሰየሙት ሲቪል ደርሶ ማርክሳውያን ሌኒናውያን ባይ መሆኑ መታወቅ አለበት። በአጠቃላይ የግራ ኃይል ርዕዩት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ቡድነኝነትም እንዲሁ በጣም ተጠናክሮ ተሰራጭቷል። የተለየ ሃሳብና አመለካከት የነበረቸውን ሁሉ እንደ ዋና ጠላትና ከሃዲ ፈርጆ የተለያዩ ቅጽሎችን ለጥፎ ቅራኖን ማስፋት፣ ጠልፎ መጣል፣ ወሬ ማናፈስ የኢሕአፓ ተብዬው ቡድን ልዩ ሙያና ተግባር ነው።

ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዩጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በውጭ አገር በአሜሪካና አውሮፓ ከሁለት ተከፍለው በተመሠረቱት ድርጅቶች መካከል ግጭቱ ስለተፋፋመ ተባብሮና ተቻችሎ በጋራ ለመሥራት ፈጽሞ ሳይቻል ቀርቷል። የመኢሶን ድርጅት የተመሠረተው በ1960 ዓ.ም በምዕራብ ጀርመን ሐምቡርግ ከተማ ሲሆን ዋና መሪው ዶክተር ኃይሌ ፊዳ ነበር። መኢሶን የትጥቅ ትግል መጀመርን አጥብቆ በመቃወም በመጀመሪያ የሕዝቡን ፖለቲካዊ ንቃት ማጎልበትና በብሔር ጥያቄም ላይ የተለየ አቋም ነበረው።

ኢሕአድ ግን በትጥቅ ትግል የኢትዩጵያን መንግሥት መጣልና ሥልጣኑን በጥቂት አብዩታውያን ምሁሮችና የላብአደር መሪነት ለመያዝ ሲያቀነቅን፣ ኢትዩጵያ የብሔረሰቦች እሥር ቤት ናት በማለት በብሔር ጥያቄ የኤርትራ ታጣቂ ተገንጣይ ኃይሎችን የመገንጠል ዓላማ ሲደግፍ የኡጋዴን

ሱማሌ ጎሣዎችም በፈፈልጉ ከሱማሌ ጋራ መዋሃድ አለበለዚያም የራሳቸውን መንግሥት የመመሥረት መብት እንዳላቸው ኢሕአድ ያምናል በማለት አቋሙን አሳውቋል።

# የየካቲት 1966 ዓ.ም አብዮት

በኢትዮጵያ በ1966 ዓ.ም በጥር ወር በሲዳሞ ነገሌ የነበረው ክፍለ ጦር አምጾ የየካቲቱ ሕዝባዊ አብዮት ተቀጣጠለ። በውጭ በሕብዕ ተድረጅተው የነበሩት ኢሕአድና መኢሶን ጎራ ለይተው በተለይም በአውሮፓ ምሽጋቸው ውስጥ ሆነው የጦፈ ቅራኔ ውስጥ ተዘፍቀው ሰፊ እንካሲላንታ ና ርስ በርስ መጠላለፍና መዘራጠጡ አይሎ በአመጽ ለመጠፋፋት አድብተው ሲጠባበቁ ድንገት ሳያስቡት አብዮቱ በነበረው ውጭያዊና ውስጣዊ ወሳኝ ሁኔታዎች ፈነዳ። ለወታደሮጡ የጠየቁት የደሞዝ ጭማሪ ቢደረግላቸውም የነዳጅና የዳቦ ዋጋ መጨመር ሳቢያ ታክሲ ነጅዎች፣ አስተማሪዎች ወዘተረፈ ሥራ አቁመው በወሩ መጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስቴር አክሊሉ ሃብተወልድ ካቢኔ በገዛ ፈቃዱ ሥራውን ለቆ የልጅ እንዳልካቸው መኮንን በመጋቢት ወር ተተካ። በዚያን ወቅት ነጻ የመገናኛ አውታሮች ተፈቅዶ ሰላማዊ የሃሳብ ክርክር ሲደርግ ነበር። ሁሉም የኅብረተሰቡ አባላት ተቃውሞዋቸውን በሰላማዊ ሰልፍና በጽሑፍ ማሰማት ተችሎ ነበር። በሚያዚያ ወር የእስላሞች ሰላሚዊ ሰልፍ አዲስ አበባን አጥለቀለቃት። የወሎና የትግሬ ርሃብ ግልጽ ተደርጎ ርዳታ ማሰባሰብ ተጀመረ። በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ተመሥርቶ ያጤውን ሥልጣን ገደበው። በዚሁ ወር በውጭ አገር በሕቡዕ ተደራጅተው የነበሩት እነ ኢሕአድና መኢሶን የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም አስበው ተንጋግተው አገር ገብተዋል።

በሌላ በኩልም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ልዩ ልዩ ቡድኖች በሕቡዕ ተደራጅተው በየካቲት ወር የተጀመረውን አብዮታዊ ሂደት እንዲስፋፋ፣ መሬት ላራሹ፣ ትምህርት ለሁሉም፣ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ወዘተረፈ. በጽሑፍና በሰላማዊ ሰልፍ ቅስቀሳቸውን አጧጡፈውት እንደነበረ የተረጋገጠ ነው።

ከውጪ መጤዎቹ ዲሞክራሲያና፣ ስፊው ሕዝብ የተሰኙትን በራሪዎች ሲያሰራጩ ያገር ውስጥ ታጋይ ቡድኖች ደግሞ፣ ቀይ ባንዲራ፣ ቀይ ኮከብ፣ አብዩት ወዘተረፈ የተባሉትን በራሪ ወረቀቶች በኅቡዕ አሰራጭተዋል። በአገር ቤት የነበሩት ዋና ዋና ቡድኖች ለምሳሌ የዩሐንስ ብርሃኔ ቡድን በአዲስ ከተማ፤ የጌታቸው ማሩ፣ የግርማቸው ለማ ኪዳኔ፣ የነ ሙሄ አብዲ ቡድን፣ የመለስ ተክሌ ወዘተረፈ ይገኙበታል።

ከውጪ የመጡት በቡደኛነት ሴራና ተንኮል የተካኑት እኔ ብቻ አውቅላችኋለሁ፣ እኔ ብቻ የሚለው ፍጽሞ ሐቅ ነው እያሉ በሕዝብ ስም የመነገድ አባዜ የተለከፉት በውሕደትና ሕብረት ፈጠራ ሽፋን ሌሎች ቡድኖችን ሁሉ ተቆጣጥረው ለጠቅላላ ውድመት ዳረጓቸዋል።

በመሆኑም ነው ጌታቸው ማሩ በአሕአፓ አንጃ ተብሎ የተገደለው የቀኃሥ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር ጸሐፊ ነበር። ግርማቸው ለማ ኪዳኔ ቀደም ብሎ የተማሪው ማኅበሩ ፕሬዘዳንት ሆኖ ያገለገልና ኋላም የሠራተኛ ማኅበር ጸሐፊ የነበረ ሲሆን ሌሎቹም ቢሆኑ ለዩኒቨርስቲው የተማሪ ማኅበር የአመራር አባል በመሆን ታላቅ ተሳትፎ የነበራቸው ሁሉ የብድኝኛነት ሰለባ ሆነዋል።

ያጤው መንግሥት ያለምንም ተቃውም ሲንኮታኮት ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም አጤ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን አውርዶ ራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ነኝ ብሎ አወጀ። የደርግ አባል ያልነበሩትን ጀግናውን ጀነራል አማን አንዶምን የደርጉ ሊቀ መንበርና ርዕሰ ብሔር አድርጎ ሾመ።

በሳምንቱ የደርጉ አባል ሻለቃ ሲሳይ ሃብቴ የሚመራ ቡድን ወደ አራት ኪሎ ሳይንስ ፋከልቲ ግቢ ባለው የኪስ ሜዳ ላይ ለተማሪዎች ገለጻ አደረጉ።

በጣም ችኩልና አፈኛ አንባራቂ ራሰ ጨብራራው መለስ ተክሌ ከሻለቃ ሃብቴ ጋራ ከፍተኛ

እስጣገባ በተለይም "ያሜሪካን ጭፍራ፣ የእስራኤል ቡችላ" እያለ የስድብ ናዳውን ሲያወርድበት የወረሞ ብሔረተኛው ሙሄ አብዲ ረጋ ባለ አንደበት የመለሰን ውርጅብኝ በመቃወም ነገሮችን አመዛዝኖ መልስ መስጠቱ ይታወሳል።
መለሰ ተክሌ ከጀብሃ ቅጥረኞች ጋራ በመሆን የአዲስ አበባን ማዘጋጃ ቤት በቦንብ ለማጋየት ያጠመዱት ፈንጂ መጠነኛ ጉዳት አድርሶ ተይዘው ደርግ የፍየል ወጠጤ አቅራራበት።

# <u>የደርግ ጭፍጨፋ</u>

"ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል መፈክር ሲያነበንብ የቆየው ደርግ በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቀንደኛ መሪነት ሕዳር 12/13 ቀን 1967 ዓ.ም 59 ሰዎችን እንበለ ፍትሕ ጨፍጭፎ በጅምላ መቃብር ቀበራቸው። ርዕሰ ብሔሩ አማን አንዶምና ሌሎች የደርግ አባላትም በግፍ ከተገደሉት ውስጥ ይገኙበታል። በሰላም እጃቸውን የሰጡት ያጤው መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት 17 ጀነራሎች፣ ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ከእሥር ቤት ተወስደው ያለፍርድ ተረሽነዋል።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዐቢይ ጉዳይ አለ። ለዚህ ፍጹም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ተጠያቂ ደርግ ብቻ ሳይሆን ሲቪል ግራ ኃይል ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ተብዬዎችም ተሳታፊዎች ናቸው።
በታሠሩት አቆርቋዥ፣ አድኃሪያን ላይ በአስቸኳይ እርምጃ ይወሰድ እያሉ ቀይ ባንዲራ፣ አብዮት፣ ዲሞክራሲያ፣ ሰፊው ሕዝብ ወዘተረፈ ቅስቀሳ አድርገዋል። አብዮት የራት ግብዣ አይደለም፤ ያለደም አብዮት የለም..... እያሉ ለደርግ አረመኔያዊ ርምጃና የኮምኒዚም ርዕዮት አቀንቃኝነት ያዘጋጁት ሲቪል ማርክሳውያንና ሌሊናውያን ተብዬ አወናባጆች ናቸው።

ደርግ የኢትዮጵያ ሕብረተሰባዊነት (Ethiopian Socialism) ብሎ ባለ 10 ነጥብ መርሃ ግብር ታሕሣሥ 10 ቀን 1967 ዓ.ም አወጀ። በእድገት ኅብረት ዘመቻ 60 ሺህ ተማሪዎች ገጠር ዘምተው ሕዝቡን ያንቁ ተባለ ሲባል የዩኒቨርስቲና የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዘመቻውን በመደገፍና በመቃወም ከሁለት ተከፈሉ። ለዚህም የመኢሶንና የኢሕአድ እጅ ነበረበት። በመጨረሻው ግን ወታደራዊ ደርግ በኃይል ስለ አስገደደ መዝመት ግዴታ ሆነ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከአማርኛ ተናጋሪዎች በስተቀር በኀሣ ተከፋፍለው ዘመቻውን ደጋፊና ተቃዋሚ የነበሩት የየራሳቸውን ውሳኔ አስተላልፈው ነበር። የትግሬና የኤርትራ ተማሪዎች ዘመቻውን የተቃወሙት በቀጥታ ወደ አገራቸው በመሄድ ሻዕቢያንና የትግሬን ነፃ አውጭ ግንባርን ተቀላቅለዋል።
በዘመቻው የተሳተፈው ክፍል ገበሬውን መሠረተ ትምህርት በማስተማርና የገበሬ ማኅበራትን በማዘጋጀት፣ የመሬት ላራሹን የየካቲት አዋጅ ተግባራዊ ለመድረግ ሞክሯል።
ቀጥሎም በሐምሌ ወር የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ከታወጀ በኋላ ዘመቻውን ለቀው እንዲመለሱ ኢህአፓ ሰፊ ቅስቀሳ አደረገ። በነገራችን ላይ ኢሕአድ እራሱን ብቸኛ የኮምኒስት ፓርቲ ነኝ ብሎ ከቆየ በኋላ ወደ ኢሕአፓ (EPRP) መጠሪያነት የተለወጠውና ፕሮግራሙን ያሳወቀውም ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም ሌሎች የአገር ውስጥ ቡድኖችን ቀስ በቀስ በማጠቃለል ነበር።

መኢሶን ደግሞ በጣም ዘግይቶ በመጋቢት ወር 1968 ዓ.ም ፕሮግራሙን አሳውቋል። ኢሕአፓ ደርጉን "ፋሽስታዊና የቡርዣዎች ደጋፊና ተባባሪ ፀረ አብዮት ነው" ሲል መኢሶን ደግሞ በተቃራኒው ከደርጉ ጋራ ተባብሮ መሥራትን መርጦ "ሒሳዊ ድጋፍ" አደርጋለሁ እያለ ሶሻሊዝምን አስተምሮታል::::
በኢሕአፓና መኢሶን መካከል በአውሮፓ የተጀመረው ጥላቻቸው ተካሮ ከመገዳደላቸው በፊት ፀረ አብዮተኛ፣ ንዕስ ከበርቴ፣ ከሃዲ፣ ቀልባሽ፣ ወዘተረፈ እያሉ ሲሰዳደቡ ከርመው ነው በቀይና ነጭ ሽብር የተጨራረሱት።

የኢሕአፓ ደጋፊዎች በአብዛኛው ተማሪዎችና አስተማሪዎች ሲሆኑ የመኢሶን ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞችና በአብዛኛው የወለጋና ሌሎች አካባቢዎች የወረሞ ተወላጆችን ያጠቃልላል።
መስከረም 10 ቀን 1968 ዓ.ም ወታደራዊ ደርግ ኢሕአፓ ተብየው በሕዝባዊ አብዮት ሽፋን ድብቅና እርቃኑን ያወጣ ሴራው ለኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች በግልጽ ይታያል፤ ከእንግዲህ ወዲያ በአናርኪስቶችም ላይ አብዮታዊ ርምጃ ይወሰዳል እያለ ለፈፈ።
ኢሕአፓ መስከረም 22 ቀን 1968 ዓ.ም የመኢሶንን መሥራችና አባል የዩኒቨርስቲ መምህር የነበረውን ዶክተር ፍቅሬ መርድን ሞዝቦልድ ሕንፃ አጠገብ በመግደል አዲስ የትጥቅ ትግል ስልት ጀመረ። ቀጥሎም ጥቅምት 28 ቀን 1968 ዓ.ም የሠራተኛ ና የማኅበራዊ ሚንስትር ጸሐፊ የነበረውን አቶ ጌትነት ዘውዱን ገደለ። ደርግ ለዚህ አጸፋ 60 አናርኪስቶችን ገድያለሁ ብሏል። በዚህ ቀውጢ ዘመን በአዲስ አበባ ኖረው ዕለት በለት ያዩትን ሁሉ መዝግበው ከድርግ ፈታሽ ወታደር የሩምታ ተኩስ ለጥቂት የተረፉት የተከበሩት ጀርመናዊ ሄልሙት ፋልከንስቶርፈር (Helmut Falkenstoerfer, Aethiopien Tragic und Chancen einer Revolution, Radius -Verlag 1986, PP. 34-42) ያቆዩልን ዝርዝር መረጃ መምልከት አስፈላጊ ነው።
የኢሕአፓ ጀሌዎች በአዲስ አበባ ከተማ ተማሪዎችና አስተማሪዎችን በሙሉ ለመቆጣጠር አስበው የሚጠረጥሯቸውን ተማሪዎችና አስተማሪዎች መስቀል፣ መደብደብ፣ በመስኮት ወርውሮ በመጣል ማሽበሩን ተያያዙት። ለምሳሌ የምኒልክ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አካለ ስንኩሉ አቶ መኮንን ሸገናውን በጠራራ ፀሐይ ቢሮ ገብተው የኢሕአፓ ነፍሰገዳዩች ጠየቁት። በተፈሪ መኮንን፣ በሽመልስ ሃብቴ፣ በአስፋው ወሰን፣ በኮከበ ጽባሕ፣ በመርካቶ ወዘተረፈ ት.ቤቶች መኢሶን ናችሁ የተባሉት ተማሪዎችና አስተማሪዎች ከመስኮት ተወርውው የሞቱና አካለ ስንኩል የሆኑትን ቤቱ ይቁጠራቸው። የሠራተኛው ማኅበር ሊቀ መንበር በየካቲት ወር ተገደለ። ጋዜጠኞች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ የቀበሌ ማኅበር ሊቀ መናብርት በያለበት ተጨፈጨፉ። በአዲስ አበባ የከተማ ፋኖነት ኢሕአፓ ሕፃናትን በነፍሰ ገዳይነት ማሰማራቱ እንኳን አያሳፍረውም። እረ! ለመሆኑ በነጭ ሽብር ሕይወታቸው የተቀጠፈው ኢትዮጵያውያን ሰማእታት አይደሉም? ስለምን የቀይ ሽብር የኢሕአፓ ሰለባዎች ብቻ "ሰማእታት" እየተባለ ይለፈፋል? የኢሕአፓ ተብዬውና በ1970 የተደመሰሰው ድርጅት መሪዎች በሕይወት ያለት እነ ክፍሉ ታደስ፣ ኢያሱ ዓለማየሁ፣ ወዘተረፈ ለፍርድ መቅረብ አለባቸው። በኢትዮጵያ ለተካሄደው እልቂትና ጭፍጨፋ ከደርግና መኢሶን ባላነሰ ተጠያቂዎች ናቸውና።

በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ቀበሌዎች ታጠቁ። በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የርስ በርሱ ጦርነቱ ተጀመረ። የሰዓት እላፊው ከምሽቱ ፩ ሰዓት ድረስ ታወጀ። የቀበሌ አብዮት ጠባቂዎች በየመንገዱ ላይ መቆጣጠሪያና መፈተሻ ኬላ አቋሙ። በመጋቢትና በግንቦት ወራት የአዲስ አበባ ቤቶች ለመዛሪያ ፍለጋ ታሰሱ። በመጀመሪያ ሌኒን በተሰየመው ቅይ ሽብር የአዲስ አበባ ና ሌሎች ከተሞች በደም ታጥበዋል። በቁጥጥር ሥር የዋሉት አስራኞች ተገርፈዋል ተሰቃይተዋል። ብዙዎቹም ሌሊት ሌሊት እየተወሰዱ ተረሸነዋል። በቀይ ሽብሩ አፍላ ወቅት በሕዳር ወር ሻላቃ አጥናፉ አባተ የደርጉ መሥራች እና ምክትል ሊቀመንበር የነበረው "አድሃሪ የኢድዩ አባል ጸረ አብዩተኛ" ተብሎ ተረሸኗል።

ኢሕአፓ በከተማ ፋኖነት ዘመቻ ቀጥሎበት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተቋቋሙት 297 ቀበሌ ማኅበራት ሊቀ መናብርት ውስጥ 148 ተገድለዋል። ደርግና አጋሮቹ እነ መኢሶን ተባብረው ኢሕአፓን በጭያረው እሳት አቃጠሉት። በግንቦት 1970 ዓ.ም ቀይ ሽብር አከተመ። ( ያው ገጽ 38)

መኢሶንም ብዙም ሳይቆይ ከደርግ ጋራ ተጣልቶ በሕብዕ ገባሁ ሲል ተደመሰሰ። ከደርግ ጋራ የተቃቃሩት በታጠቅ ጦር ሠፈር የተዘጋጀውን ብሔራዊ ጦር የሱማሌ ወረራና ሰርጎ ገብን ለመከላላከል እንዲዘምት ደርግ ሲደግፍ መኢሶን ተቃሞ ሚሊሻው በፀረ አብዩተኞችና ቀይ ሽብር ለማፋፋም ብቻ መዋል አለበት በማለቱ ነበር።

ከዚህም ሌላ ደርግ በሐረርጌ ለሚኖሮ አማሮች ራሳቸውን ከሰርጎ ገብና ከአክራሪ እስላም ቆቱዎች ሽብር እንዲከላከሉ ማስታጠቁ መኢሶንን በጣም አስኮርፎታል።

ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል ወደ አመጽና መጨፋጨፍ የቀየሩት ሲቪል ግራ ኃይል ተብዬ አስመሳይ ማርክሳውያን የነበሩት ናቸው። በተሳሳተ ርዕዩት፣ ከኢትዮጵያ ታሪካና ማኅበርሰብ ሁኔታ ጋራ በጭራሽ ግንዛቤና ተዛማጅነት በሌለው ትንታኔና የትግል ስልት ሀገሪቱን ለከፍተኛ እልቂት፣ ከባሕላዊው አስተዳደር ጉድለት እጅግ የባሰና የከፉ ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ ገብታለች።

ዛሬ የወያኔ ትግሬ የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ የግራ ኃይል ተብዬ ደርሶ ማርክሳውያን ማመሳቀል ውጤት እንጂ ድንገት የተከሰት ሁኔታ አይደለም።
የነዋለልኝ መኮንን ከሃዲና ባንዳ ፀረ ኢትዮጵያ የፋሽስቶች ጀሌ ጋጋኖ ውዳቂ ትውልድ የታሪክ ትቢያ ነው። ዋለልኝ መኮንንና ብጤዎቹ የኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ጠላት ናቸው። የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካን ጸረ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በኢትዮጵያ እንዲሰፍን አስደርገዋል።
ያ ትውልድ ደንቆሮ ጠጣ እንጂ ከቶ ማሰብ የማይችል በመሆኑ በውሸት ሶሻሊዝም ጨንበል ተሸፋፍኖ ኅሠኝነትን በማቀንቀን ሥልጣን በአቋራጭ ለመግኘት ሲስገበገብ ማኅበረሰቡን ለባሰ ችግር ዳርጎታል።
ያ ትውልድ ያራገበው "መሬት ላራሽ" የኢትዮጵያን ገበሬ በጠቅላላው ለቅጥረኛው መንግሥት ተብዬ ጭሰኝነትና ለዓለም አቀፍ የውጭ ከበርቴዎች ዘረፋ ያዘጋጀ እንጂ ምንም ጥቅም አላስገኘም።
ያ ትውልድ የኢትዮጵያን ሕዝብ እድገትና ልማት ያደናቀፈ ፍጹም ቅጥረኛ ና ተንኮለኛ ነበር፣ ነው።
ያ ትውልድ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ነፃነትና ልዑላዊነት ጠላት ሆኖ በአፉ የአሜሪካን ኢምፔሪያዝሊም ይውደም እያለ በልቡና በድርጊቱ ያማሪካን ተላላኪና አምላኪ የነበረና የሆነ ነው። ያ ትውልድ በሶሻሊዝም ሽፋን ሥልጣን ለማግኘት ቋምጦ ሲከስር የፈረጠጠው ወደ ምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ እንጂ ወደ ሩሲያና ቻይና አልነበረም። ለምን ?የፈላጭ ቆራጭ ሶሻሊዝምን አምባገነናዊ ሥርዓት በሕዝብ ትከሻ ላይ ጭነው ሊኮፈሱ የተመኙት ሳይሳካ ነው ተሰደው በምዕራቡ ዓለም የሚቆዝሙት።

ለፀረ ዐማራ ቅጥረኛ ዝምታና ይሉኝታ የለም!
ውሸት ማራግብ ይቁም!
ወንጀለኞች ለፍርድ ይቅረቡ!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር! ..................ይቀጥላል

እኔ፤ ሰንጎጎ ቀልቤሳ
የውብ ዳር ሃብታሙ
ገብሬ ጉልቱ